

# አቤት ውሸት! አቤት ውሸት!



*ወንድሙ መኰንን፣ ሎንደን መጋቢት 2003*

ወያኔ የውሸት ቋት ነው። የወያኔ ውሸት ስልችት ያለው ኢትዮጵያዊ በዕብለቱ ዙሪያ ቀልድ እየቀለደ የባዶ ሆዱ በሳቅ ያስታግሳል። አንዱ ቀልድ የ42ቱ ኢንች ጠፍጣፋ ቴለቪዢን ወያኔ በዋሸበት ቁጥር እየሸተማቀቀ፣ እየተሸማቀቀ ተኮራምቶ ወደ አንዲት ብልጭ፣ ድርግም የምትል 15 ኢንች መለወጡ ነው። ምን ወያኔ ያልዋሸው አለ? ከሻዕቢያ ጋር አብሮ የወጋ ኢኮ ነው! ምነው ቢባል፣ "ደርግን አስወግጄ ዴሞክራሲ ላመጣ ነው" አለን። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት። ድንቄም ዴሞክርሲ! አሁንም አፈናው ከደርግ የበለጠ እንጂ፣ ያነሰ አለመሆኑን እንደነቃንበት ያውቅ ይሆን?!

ወያኔና ሻዕቢያ ተባብረው አዲስ አበባንና አሥመራን ከቶቆጣጠሩ ማግስት፣ በዘር ከፋፈለን። ምነው ቢባል፣ ጭቁን ብሔረሰቦች፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚፈልጉት፣ መብታቸው ሲታወቅላቸው ብቻ ነው አለን። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! ሀቁ ወያኔ የማንንም መብት የማይጠብቅ ዘራፊ የወሮበላ መንጋ መሆኑ ነው። አንቀጽ 39ን ሕገ መንግሥቴ በሚለው ዝባዝንኬ ውስጥ የዶለውም፣ አጋሩን ተገንጣይ ሸዕቢያን ለመርዳት እንጂ ለሌሎቹ አዝኖ አልነበረም። እንዲያውም ሀቁ፣ ሌላውን "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!" የሚለውን አገር-ወዳድ "እኔ ከሌለሁ ነገ፣ ኦነግ፣ ኦብነግ እና ሌሎቹም መብታቸውን ተጠቅመው ኢትዮጵያን ይበጣጥቁአታል" እያለ ሽብር ነዝቶ ጭጭ ሊያሰኝበት፣ የተጠቀመበት መሣሪያው ነው። ሀቁ ውሎ ሳያደር ወጣ። ኤርትራን አስገነጠለ። ከኤርትራ መገንጠል በኋላ ሌሎቹን አፍንጫችሁን ላሱት አላቸው። እነዚያማ ከተገነጠሉ፣ ከየት ሊዘርፍ? ለኤርትራ ግን፣ በተባበሩት መንግስታትና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮሪዶሮች ኮሮጆ ተሸክሞ "ተገንጣይዋን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛትን "ናጽነት" ዕወቁልኝ" ብሎ የዓለም መንግስታትን አስደመመ። ዓለም ጉድ አለ። መንግሥት ወይ ድንበሩን ለማስከበር ሲዋጋ፣ ወይም ከጎረበት የኔ ነው የሚለው መሬት ለማስመለስ ሲውደቅ ሲነሳ እንጂ፣ የራሱን መሬት ቆርሶ ለባዕድ ሊሰጥ የወገኑን ድም ሲያፈስ ሲታይ ወያኔ የመጀመሪያው ሁኖ




ስዕል በተ.ጎ

ታሪክ ሠራ። "ምነው ምን ነካህ" ሲባል "ለዘላቂ ሰላም ብዬ ነው" አለን። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! - አቤት ውሸት! አቤት ውሸት (ዜማ ጨምሩበት)! ብዙም አልቆየ፣ "ወያኔ እንዲሁ አንስቶ መሬት የሚሰጥ ከሆነ፣ እስቲ ደግሞ ተጨማሪ ለም መሬት ከኢትዮጵያ ልቆንጥርና ልውሰድ" ብሎ ሻዕቢያ ባድሜን ወርሮ ያዘ። እነመለስ እና እነበረከት ሊመርቁለት ተነሱ። እነ ሥዬ፤ እነ ገብሩ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ነቁበት። "አይሆንም!" አሉ! ሻዕቢያን "ውጣ" አሉት። በመለስ የተማመነው ሻዕቢያ ግን "ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተጣላው ወያኔ ቢደነፋ የትም አይደርስም" ብሎ፤ "ኤርትራ ከባድሜ መውጣት ማለት፣ ጸሐይ አትወጣም ማለት ነው፣" ብሎ አሾፈ። እነስየ ነገሩ ገብቶአቸው የትግራይን ሕዝብ ይዘው ወደ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ "እሪ" አሉ። ሕዝብ "ሆ!" ብሎ ተነሳ።

ሻዕቢያ ከባድሜ ተበረረ። መባረር ብቻ ሳይሆን፣ "እራሱ የኤርትራ መንግሥት" ተብዬው ሕለውና አደጋ ላይ ሊወድቅ ሆነ። ሻዕቢያ እስከመጨረሻው ከተቀጣ፣ መለስ አለመትረፉን ተረዳ። የባንዳው የልጅ ልጅ መለስ ዜናዊ ጦሩ ወደፊት እንዳይገፋ ባለው ሥልጣን፣ አስቆመ። "ምነው?" ቢባል፣ "አሜሪካ ማዕቀብ ልትጥልብን ነው" አለ። ውሸታም! ቀጣፊ! አሜሪካ ጉዳይዋም አልነበር። በኢትዮጵያውያን ደም የተገኘውን ድል፣ የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ቀለበሰው። አልጀርስ ላይም ሂዶ የኢትዮጵያን ድል፣ አሳልፎ ለሻዕቢያ ሰጠ። በዚህም መቸ አበቃ። ሄግ ላይ የዓለም መንግስታት ሊዳኙ ተቀምጠው፣ ለኢትዮጵያ የፈረዱአትን ኢግላ "እንፈልጋትም፣ ድሮም የኤርትራ ግዛት ናት" አለ! ወቸ ጉድ! በጠላት እኮ ነው የምንገዛው! ያንን ሊዳኙ የተቀምጡት ሹሞች ጽፈውት ለታሪክ አስቀምጠውታል። ከዚያም የሄጉ ዳኞች ባድሜን ለኤርትራ ሰጡ። ወያኔ ዓይኑን በጨው አጥቦ፣ "ሰልፍ ውጡ! ዕልል በሉ! ባደሜ ለኛ ተሰጠች!" ብሎ ሕዝቡን አሰለፈው። እዚያ ላይ ዕውነቱን ነበር። ለእነሱ፣ ለኤርትራውያን ተሰጠች። አልተረዳነውም እንጂ። ውጭ ያለነው፣ የውሳኔውን ሰነድ በእጃችን ይዘን፣ "እዩት ይኸን ቀጣፊ! ባድሜ ለኤርትራ ተሰጥታለች። እያሞኛችሁ ነው!" ብለን ብንጮኽ፣ የሱ ውሸት፣ ከኛ የዕውነት የሕዝቡን ጆሮ አደንቁሮት ደምጻችንን ዋጠው። ስለወያኔ አፍረን ዝም አልን። ቪኦኤ የተባለው የአሜሪካን ሬዲዮ ያንን በተመለከተ የሻዕቢያውን አምባሳደር ግርማ አስመሮምንና የወያኔውን አምባሳደር ካሳሁን አየለ አነጋግሯል። እንዳለቆቹ መዋሸት ያለተሳካለት ካሳሁን አየለ ሲንተባተብ የሰማው መለስ ሆዬ ስልክ አንስቶ "አበበ ነኝ" ብሎ የወሸት ስልቻውን ሳያፍር ተረተረ። እስቲ እንስማው። http://people.famouswhy.com/meles_zenawi/። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! አፍርኩለት! የት አባቴ ልግባ!

ለማጂ ቀጣፊ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሥቃይ መለስ ዜናው መጋቢት ፴፯ ቀን ፪ሺ፫ ፓርላማዬ በሚለው በረት ውስጥ ለኮለኮላቸው ድብኝት አሻንጉሊቶቹ ሲናገር፣ ድርብ ቀመር የታየበት ዕድገት አሳይተናል ብሎ ቀባጠረ። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! ሀቁ መሬት ላይ እንደሚታየው ከሆነ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ፣ ጠሙን ዉሎ ጠሙን ያድራል። አለው የሚባል፣ ዛሬ ቁርስ ከበላ፣ ምሳን አስቦ የሚውል ዜጋ ነው። እንዲያውም ምሳና ቁርስ አንድ ላይ የመብላት ዘዴ ዘይዷል ። እሱም ምግብ ከተባለ፣ አንድ ሙዝና አንድ ቁራጭ ዳቦ ናት። ያቺም "ቁምሳ" የሚል ስም ወጥቶላታል። የወያኔ የውሸት ቱልቱላ ሲነፋባቸው ስልችት ያላቸው የኢትዮጵያ አርቲስቶች፣ "ፈረቃ" የሚል ሙዚቃዊ ድራማ አዘጋጅተው በዚያን ሰሞን አዝናኑን። ካላዩት የሚከተለውን ተጭነው http://www.youtube.com/watch?v=XpJYkJoWmIc እርስዎም ይዝናኑ።



የወያኔ ድርብ ቀመር የልማት ውጤት በተግባር ሲመነዘር ሕጻናትን ከቆሻሻ አስለቅሞ ያስበላል።

ችጋሩና ቸነፈሩ የተባበሩትን የዓለም መንግሥታት አሳስቦት "ጠኔው ድባቡን አጥልቷልና ቶሎ ለጋሽ አገሮች ካልደረሱላት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሀብ እንደ ቅጠል ሊረግፉባት ይችላሉ፤" ብለው ቅርብ ቀን ያስጠነቀቁትን ልብ ይሏል። የችግሩ ብዛት፣ ዛሬ ማንም ከሚችለው በላይ ሆኖበት፣ ቤተሰብ ብሔራዊ ውርደት ተሸክሞ፣ ትናንሽ ልጃገረዶች፣ ትምህርት ቤት ሳይሆን የሚውሉት፣ ወይ ለአስነዋሪ ተግባር ተሰማርተው በሸቀሉት ገንዘብ በተሰቦቻቸውን ለመመገብ የዚያው የወያኔ ባለሥልጣናት ፍተወት ጥማት ማርኪያነት ሲዳረጉ፣ ሌሎች እንደዝህች ልጅ ቆሻሻ ውስጥ ምግብ ፍለጋ ሲለቅሙ ነው የሚውሉት። የኛዎቹ ሀፍረተቢስ ዘመናይ ገዢዎች ታዲያ ዓይናቸውን በጨው አጥበው "በልማት ያስመዘግብነውን ዕድገት ኑ እዩልን፣ ተመልከቱልን"[1] እያሉ በደረቁ ሊላጩንን ይሞክራል። የውሸት መንፈስ የተጠናወተው ወያኔ ስላስመዘገበው የልማት ግብ ያለንዳች ሀፍረት ሲደሰኩር ከሰሙት የውጭ አገር ሰዎች መሀል፣ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ከነበሩ የጀርመን የፓርላማ ልዑካን አንዱ ሚስተር ቲሎ ሆፐ (Mr Thilo Hoppe) እንዴት አጭበርባሪዎች እንደሆኑ አጋልጠው፣ የጀርመን መንግሥት ዕርዳታውን ወደፊት ያለገደብ ከመለገሱ በፊት እንደገና የሰብአዊ መብት ረገጣውን መልሶ ማጤን እንዳለበት አሳስበዋል[2]።

---

[1] http://www.news24.com/Africa/News/Ethiopia-faces-food-shortages-20050223

[2] http://www.ethioguardian.com/news.php?extend.4347.5

በዚሁ የፓርላማ ዲስኩር፣ ይኸ ሀፍረተ ቢስ ጉደኛ ብዙ ብዙ ብሏል። አንዱ፣ ኤርትራ ላይ ወያኔ የነበረው ፖሊሲ እንደተቀየረና፣ ከአሁን በኋላ ግን የሻዕቢያን መንግሥት በኃይል ለማስወገድ እንደ ወሰነ ዘብዝቧል። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! ማ! ወያኔ ሻዕቢያን ሊገለብጥ? እንዴት ተቀለደ ጃል! ፈጣሪው ማን ሁነና ነው ወያኔ ሻዕቢያን የሚያስውግደው። በረከትና መለስ እራሳቸው ሸዕቢያዎች አይልደሉም እንዴ! እንዴት የኢትዮጵያን ሕዝብ ንቀዋል በል እነዚህ ቁጭ በሉዎች! ለመሆኑ ስብሀት ነጋ የተባለው የወያኔ ቱባ በዚያን ሰሞን ወጥቶ፣ አንድ የኤርትራን ነጻነት የሚያሰጋ ነገር ከመጣ፣ የወያኔ መንጋ በሙሉ እንደሚዋጋ እንደዘላበደ ተረሳ እንዴ! የረሳም ካለ፣ http://www.aigaforum.com/audiovideo.html ጠቁሞ መስማት ይቻላል። የራሱስ የመለስ ንግግር ቢሆን! ማን ነበር ይኸንን ንግገግር ያደረገው በኤርትራ "ናጽነት" ቀን?

http://www.fettan.com/Documents/Harvesting_of_Planted_Ethnic_Discord.pdf.

ምናልባት፣ ትግርኛው ይሻለው ይሆን? እሱማ የባሰ ነው። ጠላታችሁን አከርካሪውን ሰበረነዋል ይላል።

http://www.fettan.com/Documents/Harvesting_of_Planted_Ethnic_Discord.pdf

እንዲያ ዛሬ በፓርላማ ተበዬው ደርሶ እንዲህ ሲጨህ፣ ከያኔ አባባሉ ጋ ያወዳድረው ይሆን?! በዚያን ጊዜ ሁለት ወደቦቻችንን ሲያስረክብ፣ ዘላቂ ሰላም ላመጣ ነበር ያለው። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! በውሸት ላይ ቤቱን የመሠረተው መሰሪይ፣ ካልዋሸ ራሱን ያመዋል። ይኸውና ኢትዮጵያን ዘላቂ ጦርነት ውስጥ ዱሏት ያዳክራታል። ይኸ አሁን ኤርትራ ላይ የሚያደርገው ድንፋታ በዕውነት ኤርትራን ለመውጋት ፈልጎ ሳይሆን የምትለኮሰዋን ጦርነት ተጠቅሞ፣ ዙሪያውን እየፈነዱ ያሉት ሕዝባዊ አመጾች ደርሰውበት እንዳያጋዩት ሰግቶ የሕዝባችንን አትኩሮት ወደዚያ ሊያዞር የሸረባት ደባና መፍጨርጨር ነው። ኸረ በዚህ በበቃልን። ሌላም ብሏል።



አሁን አሁንማ የወያኔ መንጋ ለውሸቱ መቸርቸሪያ የአገር ቤቱ ገበያ ጠቦት ከአገር ውጪ ያለነውን ደግሞ ሊያደነቁር ወደ ውጪ ሊልክ፣ ወይም ኤክስፖርት ለማደረግ ቱባ፣ ቱባ ሚኒስቴሮቹን አሜሪካና አዎሮፓ አሰማርቷል። በውሸቱ ሊፈታን! ታዋቂ ሙዚቀኞች ከአገር ቤት የመጡልን ያህል ተንገብግበን፣ በየአዳራሹ ታጭቀን የወያኔ ውሸት ለመኮምከም ሰፍ ብለን የምንጠብቀው መሰሎታል። እነዚህ የወያኔ ቅጥረኞች ምን ሊሉን እንደተዘጋጁ፣ ከወዲሁ ከራሱ ከመለስ የፓርላማ ተቢዬው ዲስኩሩ ተገንዝበነዋል። እስቲ የሎንደኑን ዝግጅት እንመልከት።

አንደኛ፣ ፓርላማ ላይ "ትራስፎርሜሽ-ትራስፎርሜሽ" እያለ ሲያላዝን የነበረውን አሰልቺ ዲስኩር እዚህም ሊደግመው ማቀዱን ፖስተሩ ያጋልጠዋል። ኤዲያ! የምን ትራንስፎርሜሽን ነው? የሕዝባችንን ቁልቁል ዕድገት ቀስቱን ስቶ ሽቅብ ካላምዘግዘጉት፣ እትዮጵያ እንደሆነች፣ ከድጡ ወደማጡ ዘቅጣለች። እርግጥ የነሱ ኪስ ደልቧል። ከደደቢት በረሀ የተበጣጠቅችና እና በ12 መረፌ የተሰፋች ቁምጣ ለብሰው፣ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ከገቡ በኋላ "ትራንስፎርም" አድረገው አርማኒ ለብሰዋል። አልፎላቸዋል። በድርብ ቀመር አገሪቱ አደገች፣ ተመነደገች የሚሉን ግን፣ አንዲት ቋትም የምትሞላ ጥሬ እህል ለአገሪቷ አልተረፈትም። ላለፉት 20 ዓመታት ይኸ የኢትዮጵያ ድርብ ቀመር ዕድገት ዕውነት ቢሆን ኑሮ አገሪቱ ሽቅብ አድጋ ተመንድጋ አሜሪካን ቁልቁል ባየች ነበር። ውሸት ድሮም ነፋስ ነው። አይዘገንም።



ስዕል በተ.ጎ

“አባይን እገድባለሁ! ግብጽ ምናታባቱ!” የሚለውን አዲስ ዘፈን ይዞ ብቅ ብሏል! እንዴት ተከሰተለት እባካችሁ! አቤት ውሸት አቤት ውሸት! ሀቁ ሌላ ነው። ለነገሩ እንኳን ያንን ያሚያክል ብዙ ቢሊዬን የሚያወጣ ግድብ በራሱ ሊሠራ ይቅርና፣ የተከዜውም ግድብ ሥራ ማስኬጅያ ገንዘብ አጥሮት እንደ አባ ድንቂቱ በሬ መቀሌ ላይ ተገትሮ ቀርቷል። ውጭ ኗሪውን ኢትዮጵያዊ (ዲያስፖራውን) “ና! አብረን አባይን ገደበን፣ ግብጽን አብግነን፣ አገራችንን ከጨላማ ፈረቃ ፣ አልፈን ተርፈንም፣ ለአንጎላ ሸጠን ትርፍ በትርፍ፣ ሀበት በሀብት እንድናምነሸንሽህ፣ አንተ ብቻ ዝም ብለህ ቦንዱን በጠንካራ ምንዛሪ (hard currency) ግዛን” ነው የሚሉን። አቤት ቅጥፈት! አቤት ቅጥፈት! እስቲ አሁን “የሚሌንየሙን ግድብ” የሚያክል ነገር ከኢትዮጵያዊው በልመና በተገኘ ገንዘብ ይገነባል? አቤት ውሸት! አቤት ውሸት!። ሀቁ፣ ሌላ ነው! ኢትዮጵያዊውን ሁሉ ያስተከዘው ለተከዜው ግድብ ሥራ ማስኬጅያ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚደረግ ማውናበጃ ነውና ፣ ጎበዝ ከነዚህ ኪስ አውላቂዎች ኪሲህን ጠብቅ። ደሞ ልብ በሉ። እንዲያ ግድቡ ቢሠራ እንኳን፣ መሀል አገር ሳይሆን ሱዳን ጠረፍ ነው። ለሱዳን ቆርሶ የቸረውን መሬት የረሳ አለ? አንድ ነገር ቢፈጠር፣ መጀመሪያ የሚወድመው እሱ ነው። እንዲያው ተሳክቶ ቢገነባ፣ በሊዮን ብር ፈሶበት አልቆ ሥራ ላይ ሊውል አንድ ቀን ሲቀረው ነው ሱዳንና ግብጽ አፈር ድሜ የሚያስበሉት። የቦንዱን ዋጋ ከየት ልታሰመልሱ ነው? ደግሞ በዚህ ላይ አንቀጽ 39 አለ። ሕገመንግሥቱ ማንኛውው ክፍለ ሀገር ነገ ከኢትዮጵያ ተግንጥሎ የራሱን መንግሥት ማቋቋም ይችላል። የሰይጣን ጆሮ አይስማውና፣ ነገ የ ቤኒ ሻንጉል ግዛት መብቱን ተጠቅሞ የራሱን መንግሥት ቢመሠርት፣ የቦንዱን ክፍያ ከየትኛው መንግሥት ሊጠየቅ ነው። ወያኔ ወዳቂ ነው። በኔ ይሁንባችሁ። አብቅቶለታል። የሚመጣው መንግሥት የወያኔን ዕዳ ሊክፍል ነው ብሎ የሚያስብ ካለ፣ ጅል መሆን አለበት። ወዳጄ ልቤ፣ ሰዶ ማሳደድ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ።


ስዕል በተ.ጎ

ሌላው አጀንዳቸው ዲያስፖራው አገር ቤት ገብቶ ንዋይ እንዲያፈስ፣ በሚሰጠው አራት መቶ ካሬ ሜትር መሬት ላይ መኖሪያ ቤቱን እንዲሰራ፣ ገንዘቡን በውጭ ምንዛሬ ኢትዮጵያ ባንኮች ውስጥ እንዲያስቀምጥ ለማባበልና ለማግባባት ነው። አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! ከዚህ በፊት ጥሪቱን ቋጥሮ የገባ ሁሉ የት ደረሰ? ምን ደረሰበት! ሰንቱን ሞሸለቁትና ባዶ እጁን አስቀሩት! ሆሆይ! እኛ ከዚህ በፊት ስለዚህ ጉዳይ ብዙ፣ ብዙ ጽፈን አስጠንቅቀናል። አሁን ማን ጅል አለ፣ ጥጃውን ልጅብ አደራ የሚሰጥ? እንዲያውም እስከአሁን አገር ቤት ሄደው ቤት ሠርተው አከራየተው ውጭ የሚኖሩትን “ኪራይ ሰብሳቢዎች” እያለ በዚያ ድብኝቶቹ አሻንጉሊቶች ፊት ሲሞሽልቃቸው ሰምተናልና ተጠንቀቁ። “ወደሽ ከተደፋሽ ወያኔ ቢረግጥሽም አይክፋሽ” እንዳይሆንባችሁ። በዚህ ላይ፣ ወያኔ ገንዘባችሁን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችሁንም ጭምር ነው። “ኢትዮጵያው ውስጥ ንብረት ያላችሁ ውጭ ኗሪዎች አገር ቤት ተመልሳቸሁ፣ አሻራ ስጡ” እያለ ሲወተውት አልሰማችሁም? አሻራ ወሳጁ ፖሊስም አስከትሎ በተሰደዳችሁበት አገር መጥቶላችሁአል። አሻራህ ተወሰደ ማለት፣ ወያኔ ነብስህን በጁ ጨበጣት ማለት ነውና፣ አዳሜ አበሻ፣ መብትህን አታሰናካ! ሌላው፣ በቱኒሲያ ጀምሮ፣ ግብጽን ለጥቆ፣ ሊቢያና የመን ውስጥ የሚንቀለቀልው የሕዝባዊ አመጽ ሰደድ እሳታ ቋያ አስግቶት ነው እኛ ሳንሄድበት ሊመጣብን ያቀደው። ለሰላምም ቢሆን እኛን ሳይሆን አገር ውስጥ ከሚኖሩት ጋር ሰላም በፈጠረ። ለልማትም ቢሆን እኛን ሳይሆን እዚያው ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ወንድም እህቶቻችን ጋ ልማቱን በጀመረ። እንዲዚያማ ቢሆን እንሱ ሳይሆኑ እዚህ የሚመጡት፣ እኛ ነበር ጓዝ ጉዝጓዛችንን ሰብስበን አገራችን የምንገባው። ነገሩ የፍትህ እጦት፣ የዲሞክራሲ አለመኖር፣ የሰብዓዊ መብት መደፈር ነው እኛን ያስመረረንና ከአገራችን በአገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ጥለን እንድንሸሽ ያደረገው። እዚህ ድረስ ተከትሎና ተከታትሎ እጁ ሊያስገባን ከቻለማ፣ ሙተናላ፣ አንረባም ማለት ነው።

ይኸንን የወይኔን ባለሥልጣናት ወደ ውጭ መምጣት በተመለከተ የአሜሪካ ድምጽ፣ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል በብዙ አቅጣጫ ጭብጡን ሊያስይዘን ብዙ ጥሯል። ከወያኔ ኤምባሲ፣ የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊውንም ዋሀደ በላይን አናግሮት ነበር። ወሀደ ምን አለ መሰላችሁ።

ዋሀደ፡ “ተቃዋሚዎች የሚያነሱአቸው የራሳቸው ጉዳዮች አሉአቸው፣ ኢትዮጵያም ሁነው የሚያነሱአቸው ጉዳዮች ናቸው። በሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕጋዊ ጉዳያቸውን አቅርበው የሚፍታበት ሁኔታ የሚመቻቸበት ሕግ መንግሥትዊ ሥነ ሥርዓት ስላለ በዚያ የሚፈታ ጉዳይ ይሆናል።

Wahad Belay.mp3

አዲሱ ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ ለማቅረብ ይቻላል ነው የሚሉኝ?

ዋሀደ ይቻላል በትክክል! ይቻላል! አዎን።

አዲሱ ስብሰባ ሰላማዊ ሰልፍ ሁሉ?

ዋሃደ ይቻላል። ምንም ችግር የለውም።

አቤት ውሸት! አቤት ውሸት! ዕውነቱ ግን አለቃው መለስ ዜናዊ ያለው ነው።

**“ለመድረክ አባላት፣ በተለይም ለአንድነት አባላት፣ አንድ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ መንግስት ማየትና መስማት የተሳነው አይደለም። ማየትና መስማት የሚችል መንግስት ነው። ሰሞኑን ሽብርና አመጽን በማቀናጀት እየተጠነሰሰ ባለ ሴራ ላይ የሚሳተፈው በሙሉ ዋጋ ይከፍላል። በዚህ ጉድያ ላይ ግልጽነትና እርግጠኛነት መኖር ይኖርበታለን።”**

Mele's speech.mp3

በዚሁ ስብሰባ ላይ ነበር፣ መለስ ተቃዋሚዎችን የግብፅ ነጭ ለባሾች[3] ብሎ የሰደባቸው። አንተም አልተባልክ! ግብጽም አልነበር ለዚህ ያበቃው? ነገሩ ሌላ ነው። የሰሞኑ የውሸት ጋጋታው፣ ዛቻውና ማባበሉ እንዲህ እንዲህ የተዘበራረቀው፣ በቱኒሲያና በግብጽ የቤን አሊንና የሆስኒ ሙባረክን የአምባገነን ሥርዓቶች ከሥራቸው መንግሎ የጣለቸው ሕዝባዊ አመጽ፣ በአሁን ሰዓት ጋዳፊንና አሊ ሳላህን በሊቢያና በየመን በመናጥ ላይ ደርሶ የኢትዮጵያንም በር እያንኳኳ መሆኑ እየታየው ነው ሱሪው ውስጥ ሽንቱን ሊለቅ የተቃረበው። የት ይቀርላታል!

አሜሪካ ያሉት ወንድሞችና እህቶች በዘጠኙም ከተሞች የወያኔ ልዑካንን አሳፍረው ለመሸኘት ይኸችን ሰሞን ዝግጅታቸውን አጧጡፈዋል። ሎንደንም ተዘጋጅተንላቸዋል።




ገለል በልና ገለል አርጋቸው
ወደመጡበት ወዳገራቸው እያልን

እይዘመርን አፕሪል 16 ቀን 2011ን በጉጉት እየጠበቅነው ነው።

ቦታው ኢምፔሪያል ኮሌጅ
ቀኑ አፕሪል 16 ቀን 2011 (16th April 2011)
ሰዓት ከቀኑ8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት

ተደፍረናል ጎበዝ! ቤታችን ድረስ መጥተዋል።

እንግዲህ እዚህ ቦታ በመገኘት ተቃውሞአችንን አንድ ላይ እንግለጽ!

በቃ ማለት፣ በቃ ነው።

---

[3] http://www.voanews.com/amharic/news/Ethiopia-opposition-reaction-119345004.html